# መዝሙር ፡ ኅሩይ ።

አዘጋጅ ፡

## የተምሮ ፡ ማስተማር ፡ ማኅበር ፡

በምስካዬ፡ኅዙናን፡መድኃኔ፡ዓለም፡ቤተ፡ክርስቲያን፡
አዲስ ፡ አበባ ።

www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ ።

ልዑል ፣ እግዚአብሔር ፣ ስለሠራልንና ፣ ስለሰጠን ፣ ተስፋ ፣ ስላዘጋጀልንም ፣ አክሊል ፣ በየጊዜው ፣ በግልና ፣ በማኅበር ፣ ምስጋና ፣ እናቀርባለን ።

በማኅበርም ፣ ሆነ ፣ በግል ፣ ለልዑል ፣ እግዚአብሔር ፣ ምስጋና ፣ ከምናቀርብባቸው ፣ መንገዶች ፣ አንዱ ፣ መዝሙር ፣ ነው ። ቅዱስ ፣ ዳዊት ፣ በመጨረሻው ፣ መዝሙሩ ፣ ስለ ፣ ምስጋና ፤

ሃሌ ፣ ሉያ ።

እግዚአብሔርን ፣ በመቅደሱ ፣ አመስግኑት ፤
በኃይሉ ፣ ጠፈር ፣ አመስግኑት ።
በችሎታው ፣ አመስግኑት ፤
በታላቅነቱ ፣ ብዛት ፣ አመስግኑት ።
በመለከት ፣ ድምጽ ፣ አመስግኑት ፤
በበገና ፣ በመሰንቆ ፣ አመስግኑት ።
በከበሮና ፣ በደስታ ፣ አመስግኑት ፤
በአውታርና ፣ በእምቢልታ ፣ አመስግኑት ፤
ድምፁ ፣ መልካም ፣ በሆነ ፣ ጸናጽል ፣ አመስግኑት፤
እልልታ ፣ ባለው ፣ ጸናጽል ፣ አመስግኑት ።
እስትንፋስ ፣ ያለው ፣ ሁሉ ፣ እግዚአብሔርን ፣ ያመስግን ።

ሃሌ ፣ ሉያ ። ይላል ።

www.ethiopianorthodox.org

የተምሮ ፡ ማስተማር ፡ ማኅበር ፡ ይህን ፡ የመዝሙር ፡ መጽሐፍ ፡ ለማሳተም ፡ የወሰነው ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ እስት ንፋስ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግን፡ ባለው ፡ በመመራትና ፡ በማመን ፡ ነው ።

ሁለት ፡ ወይም ፡ ሶስት ፡ ሆናችሁ ፡ በስሜ ፡ በምትሰ በሰቡበት ፡ ከዚያ ፡ በመካከላችሁ ፡ እገኛለሁ ፤ ሲል ፡ በማቴ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቁ ፡ ፳ ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክር ስቶስ ፡ እንዳስተማረን ፤ አምላካችንን ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ተሰ ብስበን ፡ የምናመሰግንበት ፤ ኃጢዓታችንን ፡ አስታውሰን ፡ ንስሐ ፡ የምንገባበት ፤ በክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ የምንተሳሰብ በት ፤ በችግር ፤ በሕመም ፤ በስቃይ ፡ የተያዙትን ፡ ሁሉ ፡ በሕሊናችን ፡ የምናስታውስበት ፡ ሰዓት ፡ ስለሆነ ፡ እያንዳ ንዱ ፡ መዝሙር ፡ በሚሰጠን ፡ ምክርና ፡ ተስፋ ፡ እንደምን ጠቀምበት ፡ እናምናለን ።

በዚህ ፡ በመዝሙር ፡ መጽሐፍ ፡ የሚገኙ ፡ አንዳንድ ፡ መዝሙሮች ፡ ከሌሎች ፡ ማኅበሮች ፡ በፈቃድ ፡ የተገኙ ፡ ስለሆኑ ፡ ስለበጎ ፡ ፈቃዳቸውና ፡ ቸርነታቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን ።

የተምሮ ፡ ማስተማር ፡ ማኅበር ፤
በምስካዬ ፡ ኅዙናን ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም፡ ቤ/ክ
አዲስ ፡ አበባ ።

መዝሙር ፡ ፩ ፤

# ስብሰባችንን ፡ ባርክልን ፤

አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ስብሰባችንን ፡ ባርክልን ፤
ልመናችንን ፡ ተቀበለን ፡ እንድንኅናጸፈው ፡ ጸጋህን ፡
እናውቃለንና ፡ ሰፊ ፡ ችሮታህን ፤
አቤቱ ፡ ላክልን ፡ በረከትህን ።

ቅዱስ ፡ ቃልህን ፡ ሰምተን ፡ ወገኖችህ ፡ እንድ
ንሆን ፡ ምረጠን ።
ልቦናችንን ፡ እጠብልን ፡ ሕሊናችንንም ፡ አን
ጻልን ፤
የመንፈስህም ፡ ኃይል ፡ ይውረድ ፡ በላያችን ፡
አቤቱ ፡ ላክልን ፡ በረከትህን ፤
በፍቅርህ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ተጠግተን ፡ እንጠራለን ፡
ቅዱስ ፡ ስምህን ፤
ታላቁ ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ሙሉ ፡ ተስ
ፋችን ፡
እንጠብቃለንና ፡ የሰማይ ፡ መንግሥትህን ፤
አቤቱ ፡ ላክልን ፡ በረከትህን ።

www.ethiopianorthodox.org

## አባታችን ፡ ሆይ ፤

አባታችን ፡ ሆይ ፡ የምትኖር ፡ በሰማይ ፤
መንግሥትህ ፡ ትምጣልን ፡ ክብርህን ፡ እንድናይ ፤
ክብርህን ፡ እንድናይ ።

ፈቃድህ ፡ በሰማይ ፡ ሕይወት ፡ እንደሆነ ፡
እንዲሁም ፡ በምድር ፡ ሰላምን ፡ ስጠነ ፡
ሰላምን ፡ ስጠነ ።

ስጠነ ፡ ለዛሬ ፡ የዕለት ፡ ምግባችንን ፤
በደላችንንም ፡ ይቅር ፡ እንድትለን ፤
ይቅር ፡ እንድትለን ።

ጌታ ፡ ሆይ ፡ አታግባን ፡ ከክፉ ፡ ፈታና ፤
አንተ ፡ ካልረዳኸን ፡ ኃይል ፡ የለንምና ።
ኃይል ፡ የለንምና ።

ኃይልና ፡ ምስጋና ፡ መንግሥትም ፡ ያንተ ፡ ናት ፤
አሜን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይሁንልን ፡ ዕረፍት ።
ይሁንልን ፡ ዕረፍት ፤



## የእመቤታችን ፡ ምስጋና ፤

የሲና ፡ ቁጥቋጦ ፡ የለመለምሽው ፤
እሳቱን ፡ ታቅፈሽ ፡ እንደምን ፡ ቻልሽው ።

የሰሎሞን ፡ መቅደስ ፡ ያብርሃም ፡ ድንኳን ፤
ባንቺ ፡ ተዘረጋ ፡ የእሳት ፡ ዙፋን ።

የእንባቆም ፡ ተራራ ፡ የሙሴ ፡ ጽላት ፤
ከአንቺ ፡ ተወለደ ፡ የዓለም ፡ ሕይወት ።

የአሮን ፡ እመቤት ፡ ዳግማዊት ፡ ሰማይ ፤
ካንቺ ፡ ተገኘልን ፡ የሕይወት ፡ ፀሐይ ።

የዳዊት ፡ መሰንቆ ፡ የኢያሱ ፡ ሐውልት ፤
ባንቺ ፡ ተቀረፀ ፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ።

የይሁዳ ፡ ንግሥት ፡ ማርያም ፡ ምሥራቅ ።
መገኛ ፡ ሆንሽልን ፡ ለፀሐየ ፡ ጽድቅ ።

ስምሽና ፡ ግብርሽ ፡ ስለተቀደሰ ፤
የኃጢአት ፡ ሰንሰለት ፡ ባንቺ ፡ ተበጠሰ ።

ስለተነገረ ፡ ቀድሞ ፡ በትንቢት ፤
ባንቺ ፡ ተሰረዘ ፡ የማይሻር ፡ ሞት ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## የዘመናት ፡ ጌታ ፡

የዕለት ፡ የዓመት ፡ የዘመናት ፡ ጌታ ፤
ከዚህ ፡ ካደረስከኝ ፡ ዘመኔን ፡ ሳትገታ ።
አቀርብልሃለሁ ፡ የክብር ፡ ሰላምታ ።
ኑ ፡ እናመስግን ፡ ከልባችን ፡ የሰማዩን ፡ አባታችን፤
ከዚህ ፡ ዕለት ፡ ከዚህ ፡ ዓመት ፡ ላደረሰን ፡ ሁላችንን ።
የሰው ፡ ልጆች ፡ ዕድሜ ፡ ጥንቱንም ፡ ሲጀመር ፤
ምን ፡ ቢወጣ ፡ ቢወርድ ፡ ቢበዛ ፡ ቢደመር ።
አንድቀን ፡ አይሞላም ፡ እንዳንተ ፡ አቆጣጠር ።

ኑ ፡ እናመስግን ፡ ...............
ስለዚህ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ ቅዱስ ፡
ነው ፤
ወዳንተ ፡ እንዲመለስ ፡ ቀን ፡ የሰጠኸው ፡ ሰው ፤
ደካማ ፡ ነውና ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ከራበው ።

ኑ ፡ እናመስግን ፡ ...............
እጅግ ፡ አደንቃለሁ ፡ የአምላክን ፡ ጥበብ ፤
ምድርን ፡ በአበባ ፡ ሰማዩን ፡ በኮከብ ፤
እንዳሸበረቃት ፡ አስተውዬ ፡ ሳስብ ።

ኑ ፡ እናመስግን ፡ ...............
በከንቱ ፡ ጊዜአችን ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳይጠፋ ፤
በርትተን ፡ ከሠራን ፡ ያላንዳች ፡ ነቀፋ ፤
አምላክ ፡ የሚሰጠን ፡ አለን ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ።

ኑ ፡ እናመስግን ፡ ...............
ከቶ ፡ ካሳለፍኩት ፡ ጊዜዬን ፡ በዋዛ ፤
ምን ፡ ያደርግልኛል ፡ ዘመኑ ፡ ቢበዛ ፤
ደግሞም ፡ በጠቅላላ ፡ ዓለምን ፡ ብገዛ ።



## ደስ ፡ ይበለን ፡

በረቂቁ ፡ ምሥጢሩ ፡ በማይሻር ፡ ቃሉ ፤
ሥጋ ፡ ተዋህዶ ፡ ከፍጡር ፡ አካሉ ።
የነገሥታት ፡ ጌታ ፡ ቤዛ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፤
መድኅን ፡ ተወለደ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ።
ደስ ፡ ይበለን ፡ ሁላችን ፤
ደስ ፡ ይበለን ፡ ተወለደ ፡ ጌታችን ።
ሰማይና ፡ ምድር ፡ የማይወስኑት ፤
ፈጣሬ ፡ ፍጡራን ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ።
ከልዑል ፡ መንበሩ ፡ ከዙፋኑ ፡ ወርዶ ፤
ትሕትናን ፡ ሰበከ ፡ በበረት ፡ ተወልዶ ፡
ደስ ፡ ብሎናል ፤
ተራሮች ፡ ዘለሉ ፡ ሊያመሰግኑት ፤
ዕፀዋት ፡ ሳይቀር ፡ የዱር ፡ አራዊት ፤
ቀላያትም ፡ ሆኑ ፡ ማርና ፡ ወተት ፤
ዕፁብ ፡ ነው ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ የጌታ ፡ ልደት ።
ደስ ፡ ይበለን ፡ ...........
አዳም ፡ ተሳስቶ ፡ ሆኖ ፡ በደለኛ ፡
ሲኖር ፡ በገሃነም ፡ በሲኦል ፡ ቁራኛ ።
አምስት ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፤
ሲፈጸም ፡ አዳነው ፡ በሰጠው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፤
ደስ ፡ ብሎናል ።
ፍዳ ፡ ሞትን ፡ ፍቆ ፡ ጽድቅን ፡ አበሰረ ፤
ሰይጣን ፡ ድል ፡ ተነሣ ፡ መርገምም ፡ ተሻረ ፤
አራቀልን ፡ ከኛ ፡ ቁጣን ፡ በትዕግሥቱ ፤
ታላቅ ፡ ነው ፡ ከሁሉ ፡ የጌታ ፡ ልደቱ ።
ደስ ፡ ይበለን ፡ ...........
(ከቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ መርሐ ፡ ዕውራን ፡ ት/ቤት ፡)

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፮ ፤

## ንጉሥ ፡ ተወለደ ፡

ንጉሥ ፡ ተወለደ ፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ፤
መርገምን ፡ መለሳት ፡ ወደ ፡ ሥርየት ፤
ሔዋንን ፡ አወጣት ፡ ከሲኦል ፡ እስራት ።
ባለግምጃ ፡ ጥላ ፡ ሆነች ፡ እመቤት ።

እሱ ፡ ባይወለድ ፡ መድኃኒታችን ፤
እሱ ፡ ባይወለድ ፡ ቸሩ ፡ አባታችን ፤
አትገኝም ፡ ነበር ፡ ገነት ፡ ምድራችን ፤

ሰላም ፡ ለእናንት ፡ ይሁን ፡ በዚህ ፡ ላላችሁ ፤
የክርስቶስን ፡ ቃል ፡ እንደሰማችሁ ።
የሕይወት ፡ ደስታ ፡ የተስፋ ፡ መሠረት ፤
አንድነት ፡ ይስጣችሁ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አባት ።

እሱ ፡ ባይወለድ ፡ …………

ገና ፡ በሕጻንነት ፡ ሃይማኖት ፡ ሲጀመር ፤
አስደሳች ፡ ይሆናል ፡ ለኋለኛው ፡ ተግባር ።
በርቱና ፡ እናጥና ፡ ሃይማኖታችንን ፤
ክርስቶስ ፡ ሰጥቶናል ፡ ዓለም ፡ አዲስን ።

እሱ ፡ ባይወለድ ፡ …………

በልጅነት ፡ ሰዓት ፡ ብዙ ፡ የደከመ ፤
ዋጋውም ፡ ከፍ ፡ አለ ፡ ዕድሜው ፡ እረዘመ ።
አይዟችሁ ፡ ወጣቶች ፡ እንሥራ ፡ በዕድሜአችን ፡
ክርስቶስም ፡ ሙቷል ፡ ለኃጢአታችን ።

መዝሙር ፡ ፯ ፤

## ሐዲጎ ፡ ተስዓ ፡

ሐዲጎ ፡ ተሰዓ ፡ ወተሳተ ፡ ነገደ ፡ ነገደ ፤
ሐዲጎ ፡ ተሰዓ ፡ ወተሳተ ፡ ነገደ ፡ ነገደ ፡
ማዕከለ ፡ ባሕር ፡ ማዕከለ ፡ ባሕር ፡ ማዕከለ ፡
ባሕር ።

ማዕከለ ፡ ባሕር ፡ ቆመ ፡ ማዕከለ ፡ ለባሕር ።

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፰ ፤

## አስተርአየ ፡ ገሃደ ፡

አስተርአየ ፡ ገሃደ ፡ አስተርአየ ፤
አስተርአየ ፡ ገሃደ ፡ አስተርአየ ።

እንዘ ፡ ሕጻን ፡ እንዘ ፡ ሕጻን ፡ ልህቀ ፡ እንዘ ፡
ሕጻን ።

ልሕቀ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ተጠምቀ ።

መዝሙር ፡ ፱ ፤

## ከመቶ ፡ በግ ፡ አንዱ ፤

ከመቶ ፡ በግ ፡ አንዱ ፡ ቢጠፋ ፡ አዳም ፤
ሊፈልገው ፡ መጣ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ።

ባገኘውም ፡ ጊዜ ፡ በጣሙን ፡ ደስ ፡ ብሎት ፤
ወደ ፡ ቀድሞው ፡ ቦታ ፡ ሄደ ፡ ተሸክሞት ።

ቸሩ ፡ እረኛችን ፡ ሆይ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤
በቶሎ ፡ ፈልገን ፡ ወዳንተ ፡ እንድንመለስ ።

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፲ ፤

## እሰይ ፡ ተወለደ ፡

እንዴት ፡ የበዛ ፡ ነው ፡ የአምላክ ፡ ቸርነቱ ፤
ኃልቶ ፡ ሳይታየው ፡ ፍጹም ፡ መሳሳቱ ።
የሰው ፡ ፍቅር ፡ ስቦት ፡ ከታላቅ ፡ ዙፋኑ ፤
ወደ ፡ ዓለም ፡ መምጣቱ ፡ በአካል ፡ መወሰኑ ።
ደስታችን ፡ ይብዛ ፡ እንዘምር ፡ በልልታ ፤
ክብርን ፡ ላወረሰን ፡ ለምሕረቱ ፡ ጌታ ።
በዓለም ፡ ተሰበከ ፡ የምሕረት ፡ አዋጅ ፤
ተወልዶ ፡ ሲጠመቅ ፡ በዮሐንስ ፡ እጅ ።
ተወለደ ፡ እሰይ ፡ ተጠመቀ ፡ እሰይ ፡ ለማዳን ፡
እኛን ፡
ተወለደ ፡ እሰይ ፡ ተጠመቀ ፡ እሰይ ፡ ለማዳን ፡
እኛን ።
በደላችንን ፡ ሽሮ ፡ ወልዶን ፡ በልደቱ ፤
አነጻን ፡ ከእድፍ ፡ በማዩ ፡ ጥምቀቱ ።
ዮርዳኖስም ፡ ሲሸሽ ፡ ባሕርም ፡ ስትፈራ ፤
በውሀ ፡ ታጠበ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መከራ ።
ደስታችን ፡ ይብዛ ፡ እንዘምር ፡ በልልታ ፤
ክብርን ፡ ላወረሰን ፡ ለምሕረቱ ፡ ጌታ ።
ባለም ፡ ተሰበከ ፡ የምሕረት ፡ አዋጅ ፤
ተወልዶ ፡ ሲጠመቅ ፡ በዮሐንስ ፡ እጅ ።
ተወለደ ፡ እሰይ ፤ ...........
(ክቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ መርሐ ፡ ዕውራን ፡ ት/ቤት ፡)

መዝሙር ፡ ፲፩ ፤

## የዓለምን ፡ በደል ፤

የዓለምን ፡ በደል ፡ የሰውን ፡ ግፍ ፡ አይቶ ፤
ዘጠና ፡ ዘጠኙን ፡ መላእክትን ፡ ትቶ ፤
ጽድቅን ፡ ለመፈጸም ፡ በደልን ፡ አጥፍቶ ።
የሰላሙ ፡ መሪ ፡ የሰላሙ ፡ ዳኛ ፤
አምላክ ፡ ተወለደ ፡ ተጠመቀ ፡ ለኛ ፡
የሰማዮች ፡ ሰማይ ፡ የማይችለው ፡ ንጉሥ ፤
ተወልዶ ፡ ሲጠመቅ ፡ እኛን ፡ ለመቀደስ ፤
ተራሮች ፡ ደንግጠው ፡ ዘለሉ ፡ እንደ ፡ ፈረስ ።
የሰላሙ ፡ መሪ ፡ ..............
ባሕር ፡ ተጨነቀች ፡ ጠበባት ፡ መሬቱ ፤
ዮርዳኖስም ፡ ሸሸ ፡ አልቆመም ፡ ከፊቱ ፤
እንደተናገረው ፡ ዳዊት ፡ በትንቢቱ ።
የሰላሙ ፡ መሪ ፡ ..............
ልጁ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ጽድቅን ፡ ሲመሠርት ፤
መጣ ፡ በደመና ፡ ሰማያዊው ፡ አባት ፤
እየመሰከረ ፡ የልጁን ፡ ጌትነት ።
የሰላሙ ፡ መሪ ፡ ..............
ባሕር ፡ ስትጨነቅ ፡ ተራራው ፡ ሲጨፍር ፤
ሰማዩ ፡ ሲከፈት ፡ ደመናው ፡ ሲናገር ፤
ዓለም ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ አየች ፡ ይህን ፡ ምሥ
ጢር ።
የሰላሙ ፡ መሪ ፡ ..............
እንደምናነበው ፡ በወንጌል ፡ ተጽፎ ፤
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታየ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አርፎ ፤
በርግብ ፡ ምሳሌ ፡ ክንፉን ፡ አሰይፎ ።
የሰላሙ ፡ መሪ ፡ ..............

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፲፪ ፡

## የጥምቀት ፡ መዝሙር ፤

አዳምን ፡ ያልተወው ፡ እንደ ፡ ተሰደደ ፤
እሰይ ፡ የምሥራች ፡ ዛሬ ፡ ተወለደ ፤

አምላካችን ፡ መድኃኒታችን ፤
ተወለደ ፡ ለነጻነታችን ፡ ለነጻነታችን ።

አዳምን ፡ ያልተወው ፡ እንደተጨነቀ ፤
እሰይ ፡ የምሥራች ፡ ዛሬ ፡ ተጠመቀ ።

አምላካችን ፡ ...............

አዳምን ፡ ለመጥራት ፡ የመጣው ፡ ሙሽራ ፤
በገሊላ ፡ መንደር ፡ ለሠርግ ፡ ተጠራ ፤

አምላካችን ፡ ...............

ሠርግቤት ፡ እንዳለ ፡ በክብር ፡ ተቀምጦ ፤
የወይን ፡ ጠጅ ፡ ሆነ ፡ ውሃው ፡ ተለውጦ ።

አምላካችን ፡ ...............

በገሊላ ፡ አውራጃ ፡ ይህን ፡ ታምር ፡ ሠራ ፡
እጅግ ፡ ያስደንቃል ፡ ያምላካችን ፡ ሥራ ።

አምላካችን ፡ ...............

ጌታችን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ያደረገው ፡ ታምር ፤
ሲያስደንቅ ፡ ይኖራል ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ፍጡር ።

አምላካችን ፡ ...............

መዝሙር ፡ ፲፫ ፡

## ሆሣዕና ፡

ሆሣዕና ፡ በአርያም ፤
ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

መድኃኒት ፡ መጣልን ፡ ለሁላችንም ፡
ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

ምሥጋና ፡ ይድረሰው ፡ ለአምላክ ፡ በመላው ፡ ዓለም ።

ሆሣዕና ፡ በአርያም ።

ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

ብሩክ ፡ ነው ፡ የመጣው ፡ በጌታ ፡ ስም ፡
ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

እናከብረዋለን ፡ ከልባችን ፡ ለዘለዓለም ፡
ሆሣዕና ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፲፬ ፤

## የስቅለት ፡ መዝሙር ፡

ፀሐይም ፡ ጨለመች ፡ ጨረቃም ፡ ደም ፡ ሆነች ፤
ያልበደለው ፡ ንጉሥ ፡ ተሰቅሎ ፡ ስላየች ።

ዋ ፡ እኔን ፡ ዋ ፡ እኔን ፤ ለኛ ፡ ይገባል ፡ ለቅሶ ፤
በኛ ፡ በደል ፡ እሱ ፤ አካላቱን ፡ ክሶ ።

ጠላቶቹን ፡ ሁሉ ፡ ከማጥፋት ፡ ታግሶ ፤
እነሆ ፡ ተሰቅሏል ፡ ከለሜዳ ፡ ለብሶ ።

ክርስቶስ ፡ ንጹሕ ፡ ሲሆን ፡ ቅዱስ ፡ ሲሆን ፡
ሐሰት ፡ ሳይኖር ፡ በቃሉ ፤
እነሆ ፡ እዩት ፡ ተሰቅሎ ፡ ደሙ ፡ ይዘንባል ፡ከካሉ ፤
የሚያምንበትን ፡ ሰው ፡ ሊያድነው ፡ ነው ፡አሉ ፤
ቢዞሩው ፡ ነውና ፡ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ።

ስለኛ ፡ ተሰቀለ ፡ እንዲሁም ፡ ሞተልን ፡
በበደልነው ፡ ክሶ ፡ እኛን ፡ ሊያድነን ።

ፀሐይም ፡ ጨለመች ፡ ............

መዝሙር ፡ ፲፭ ፤

## አምላክ ፡ ለኛ ፡ ብሎ ፤

አምላክ ፡ ለኛ ፡ ብሎ ፡ ቢያፈሰው ፡ ደሙን ፤
ለምን ፡ ከለከለች ፡ ፀሐይ ፡ ብርሃኗን ።
የከበረው ፡ ሥጋ ፡ የከበረው ፡ ደም ፤
በመስቀል ፡ ላይ ፡ ዋለ ፡ በኢየሩሳሌም ።

እዩት ፡ ኢየሱስን ፡ መስቀሉ ፡ ማማሩ ፤
ለተመራመረው ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ምሥጢሩ ፤

ቢመቱት ፡ ቢሰቅሉት ፡ ቢያላግጡበት ፤
ምንም ፡ አላገኙም ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ ስሕተት ፤
ፈጣሪ ፡ መሆኑን ፡ ምሥጢሩ ፡ ገብቷት ፤
ጌታን ፡ አልዩዝ ፡ አለች ፡ ግሁዢ ፡ መሬት ።
እዩት ፡ ኢየሱስን ፡ ...............

ይኸ ፡ ትልቅ ፡ ንጉሥ ፡ ሲገለጽ ፡ በሰማይ ፤
የናቁት ፡ የወጉት ፡ ይሉሉታል ፡ ዋይ ፡ ዋይ ።
ምድርና ፡ ሰማይ ፡ ከፊቱ ፡ ሲሸሹ ፤
ወዮት ፡ ልግባ ፡ ይላል ፡ ትልቁ ፡ ትንሹ ።
እዩት ፡ ኢየሱስን ፡ ...............

ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያረገው ፡ የከበረው ፡ ሥጋ ፤
ዳግመኛ ፡ መምጣቱን ፡ ሁላችን ፡ እንዘንጋ።
በሰማይ ፡ ለሚኖር ፡ ቅዱስ ፡ አባታችን ፤
ምሥጋና ፡ ይድረሰው ፡ ከኛ ፡ ከሁላችን ።
እዩት ፡ ኢየሱስን ፡ ...............

(ከሙሉ ፡ ወንጌል ፡ አማኞች ፡ ማኅበር) ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## የትንሣኤ ፡ መዝሙር ፡

ተገርፎ ፡ ተሰቅሎ ፡ የሞተው ፡ አንበሳ ፤
ተገንዞ ፡ በጨርቅ ፡ ተቀብሮ ፡ እንደሬሳ ።
በሞት ፡ እጅ ፡ ተይዞ ፡ አልቀረም ፡ ተነሣ ።

እናምናለን ፡ ትንሳኤህን ፤
በሥልጣንህ ፡ መነሣትክን ፤
አርአያ ፡ ነውና ፡ ለሁላችን ፡

አፈር ፡ ቢረበረብ ፡ ሣጥን ፡ ቢደረደር ፤
ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ደግሞም ፡ ቢነባበር ፤
ምድር ፡ አልቻለችም ፡ አምላክን ፡ ለመቅበር ።
እናምናለን ፡ ............

አምላክ ፡ ስትነሣ ፡ ፈርሶ ፡ መቃብሩ ፤
ሴቶች ፡ ትንሣኤህን ፡ ደፍረው ፡ ተናገሩ ፤
እንሞታለን ፡ ብለው ፡ ማንንም ፡ ሳይፈሩ ።
እናምናለን ፡ ............

እንግዲህ ፡ አልፈራም ፡ ሞትና ፡ ኩነኔ ፤
አምላክ ፡ ከሞተልኝ ፡ ተሰቅሎ ፡ ስለኔ ፤
ተደምስሷልና ፡ የሞት ፡ ሥልጣኔ ።
እናምናለን ፡ ............



## በጎቼን ፡ አውቃለሁ ፡

በጎቼን ፡ አውቃለሁ ፡ እነሱም ፡ ያውቁኛል ፤
ድምጼን ፡ እየሰሙ ፡ ይከታተሉኛል ።

ወደ ፡ በጎች ፡ ሥፍራ ፡ ያልገባ ፡ በደጅ ፤
ጻድቅ ፡ አይባልም ፡ ቀማኛ ፡ ነው ፡ እንጅ ።

በኔ ፡ የገባ ፡ ግን ፡ በቀጥተኛው ፡ በር ፤
ሕይወት ፡ ይካፈላል ፡ በላይኛው ፡ አገር ።

ቸር ፡ ጠባቂ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብንደኛ ፡ ያይደለሁ ፤
ለበጎቼ ፡ ቤዛ ፡ ራሴን ፡ የለወጥሁ ።

(ከመራዊት ፡ ክርስቶስ ፡ ማኅበር) ።

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፲፰ ፤

## ልባችሁ ፡ አይደንግጥ ።

ልባችሁ ፡ አይደንግጥ ፡ እኔንም ፡ እመኑ ፤
ብዙ ፡ ቦታ ፡ ሞልቷል ፡ አብን ፡ ብትለምኑ ።

ብዙ ፡ ቦታስ ፡ ባይኖር ፡ በላይኛው ፡ አገር ፤
ከብዙ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ የለም ፡ ባልሁ ፡ ነበር ።

እሰጣችኋለሁ ፡ ሰላሜን ፡ በብዙ ፤
በደሜ ፡ ታጥባችሁ ፡ ጽድቅን ፡ እንድትገዙ ።

ናፍቃችሁ ፡ እንደሆን ፡ ወደአብ ፡ ለመሄድ ፤
እኔ ፡ አለሁላችሁ ፡ ቀጥተኛው ፡ መንገድ ።

ተመስገን ፡ ጌታችን ፡ ከዚህ ፡ ያደረስኸን ፤
ቀንበር ፡ ባርነትን ፡ ሰባብረህ ፡ ጣልህልን ።

(ከሠራዊተ ፡ ክርስቶስ ፡ ማኅበር) ።

መዝሙር ፡ ፲፱ ፡

## ከክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ የሚለየን ፡ ማነው ፡

ከክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ የሚለየን ፡ ማነው ፡
ኀዘንና ፡ ስደት ፡ ወይስ ፡ መራቆት ፡ ነው ።
የሰማይ ፡ ቤታችን ፡ ኢየሱስ ፡ የሠራው ።
ማንቡ ፡ ንጹሕ ፡ ውሀ ፡ መሠረቱ ፡ ደም ፡ ነው ።

ሳይነጋ ፡ ተራምደን ፡ እንግባ ፡ በጧት ፤
በደሙ ፡ መሥርቶ ፡ ከሰራልን ፡ ቤት ፤
ከቶ ፡ የት ፡ ይገኛል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ቤት ፡
የውሀ ፡ ግድግዳ ፡ የደም ፡ መሠረት ።

(ከሠራዊተ ፡ ክርስቶስ ፡ ማኅበር) ።

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፳ ፡

## አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤

ሱራፌል ፡ ኪሩቤል ፡ ሱራፌል ፡ ኪሩቤል ፡ የሚሸከሙት ፤
ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ የሚሰግዱለት ፤
አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ መገኛው ፡ የፍጥረት ፤
መድኅን ፡ ተወለደ ፡ በተድላ ፡ መለኮት ፤
እነኢሳይያስ ፡ ስም ፡ ያወጡለት ፤
በተለየ ፡ አካሉ ፡ ከሦስት ፡ አካላት ።
ቃል ፡ ክርስቶስ ፡ ሆነ ፡ ቃል ፡ ክርስቶስ ፡ ሆነ ።
ስለ ፡ ሰው ፡ ድኅነት ።
አንድ ፡ አካል ፡ ...............

መዝሙር ፡ ፳፩ ፡

## ቃል ፡ ሥጋ ፡ ለበሰ ፡

ከሦስት ፡ አካል ፡ አንዱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ለበሰ ፤
ማረን ፡ ማረን ፡ ማረን ፡ ማረን ፡ ማረን ፤ ማረን ፤
አዳም ፡ በበደለ ፡ መድኃኔዓለም ፡ ካሰ ፤
ማረን ፡ ማረን ፡ ማረን ፡ ማረን ፡ ማረን ፡ ማረን ፤
በኛ ፡ ኃጢአት ፡ እርሱ ፡ ተከሰሰ ።
ማረን ፡ ይቅር ፡ በለን ፤
ሁሉን ፡ የምታውቅ ፡ የዓለም ፡ ጌታ ።
እግዚአ ፡ እግዚአ ፤
አልፋና ፡ ኦሜጋ ፡ የዓለም ፡ ቤዛ ፡ የዓለም ፡ ፈውስ፡
እግዚአ ፡ እግዚአ ፤
ሞትን ፡ አጠፋልን ፡ ሰጠን ፡ አዲስ ፡ ሕይወት ፤
ማረን ፡ ...............
ባለ ፡ ተስፋ ፡ አረገን ፡ ለዘላለም ፡ ንብረት ።
ማረን ፤ ...............
በደሙ ፡ ዋጀልን ፡ አዲስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።
ማረን ፡ ይቅር ፡ በለን ፡
ሁሉን ፡ የምታውቅ ፡ የዓለም ፡ ጌታ ፤
ተወቀሰ ፡ ቆሞ ፡ ከጲላጦስ ፡ ደጃፍ ።
ማረን ፡ ...............
ከትዕግሥት ፡ በቀር ፡ አላለየም ፡ ጸያፍ ፤
ማረን ፡ ...............
አምላክ ፡ በመሆኑ ፡ አነጻን ፡ ከእድፍ ።
ማረን ፡ ይቅር ፡ በለን ፡
ሁሉን ፡ የምታውቅ ፡ የዓለም ፡ ጌታ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡

ልዑል ፡ ክቡር ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፡ አማልክት ፤
የገዢዎች ፡ ገዢ ፡ የፍጡራን ፡ ሕይወት ።
ዘለዓለማዊ ፡ ነህ ፡ እንከን ፡ የሌለብህ ፤
የደካሞች ፡ ጉልበት ፡ የድሆች ፡ ሀብት ፡ ነህ ፡
ቸሩ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ምሥጋና ፡ ይድረስህ ።

አይመረመርም ፡ ረቂቁ ፡ ባሕርይህ ፤
ሥልጣንህ ፡ ኃይለኛ ፡ ሰፊ ፡ ነው ፡ መንግሥትህ ።
የፍቅር ፡ መገኛ ፡ የሰላም ፡ ባለቤት ፤
ለተጎዱ ፡ አሳቢ ፡ ለችግር ፡ ረድኤት ፡
ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ አማልክት ።

መላእክት ፡ በሙሉ ፡ ያገለግሉሃል ፡
ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ ያመሰግኑሐል ።
ፍርድህ ፡ ሕፀፅ ፡ የለው ፡ የማይቃወስ ፤
ምህረትህ ፡ መድኃኒት ፡ ሕይወት ፡ የሚያድስ ፡
እንዳንተ ፡ አምላካችን ፡ ማን ፡ አለ ፡ ቅዱስ ።



## ስብሐት ፤

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ስብሐት ፡ ለወልድ ፡ ስብሐት ፡ ለመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፤
ለአብና ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡
ምስጋና ፡ ከማቅረብ ፡ ከቶ ፡ አንወሰንም ።
ዛሬም ፡ ወደፊትም ፡ ዳግምም ፡ ለዘላለም ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ..............

ከዚህ ፡ ከማራኪው ፡ ከኃላፊው ፡ ዓለም ፡
የጠራ ፡ ይድናል ፡ የፈጣሪውን ፡ ስም ፡
በውነት ፡ ያለሐሰት ፡ ያለጥርጥርም ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ..............

ከቶ ፡ መድኃኒቱን ፡ የሚጠላ ፡ የለም ፡
ኑሮአችን ፡ እንዲያምር ፡ አንድነታችንም ፡
ሊኖረን ፡ ይገባል ፡ ፍቅርና ፡ ሰላም ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ..............

አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ እንለምንሃለን ፡
እንድትገኝልን ፡ በመካከላችን ፤
ይኸው ፡ ተገኝተናል ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ሆነን ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ..............

ያልከውን ፡ አስበህ ፡ እናንተ ፡ ሁላችሁ ፤
ስሜን ፡ ከጠራችሁ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ሁናችሁ ፤
እኔም ፡ እገኛለሁ ፡ በመካከላችሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፳፱ ፤

## በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፤

በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ፍጡር ፤
በግልጽ ፡ ይመልከተው ፡ ይህን ፡ የምላክ ፡ ታምር።

አምላካችን ፡ መድኃኒታችን ፤
ምስጋና ፡ ይድረስህ ፡ ከዚህ ፡ ላደረስከን ።

የተንበረከከው ፡ የይሁዳ ፡ አንበሳ ፤
ጠላትን ፡ አድቅቆ ፡ ድል ፡ አርጎ ፡ ተነሣ ።
ስለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሥቃይ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የኛ ፡ ካሣ ።

አምላካችን ፡ ...............
መርዝ ፡ ቢረጭብን ፡ ቢዘንብብን ፡ እሳት ፤
በአርበኞቻችን ፡ ደም ፡ አግኝተናል ፡ ሕይወት ።

አምላካችን ፡ ...............
ደመና ፡ አጥንታቸው ፡ አጥር ፡ የሆነላት ፤
እናት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተነሣች ፡ በኩራት ።

አምላካችን ፡ ...............

መዝሙር ፡ ፳፰ ፡

## ተነሡ ፡ እንዘምር ፡

ተነሡ ፡ እንዘምር ፡ ተነሡ ፡ እንዘምር ፤
ተነሡ ፡ እንዘምር ፡ ላምላክ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፤
ሁላችንም ፡ እንጂ ፡ ወንድ ፡ ሴት ፡ አንበል ፤
ተነሡ ፡ እንዘምር ፡ ላምላክ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፤
የአምላክ ፡ ምስጋና ፡ ምን ፡ ያሳፍራል ፤
እንኳንስ ፡ እሱና ፡ ሰው ፡ ይመሰገናል ።

ተነሡ ፡ እንዘምር ፡ ...............
ለሚያወርድልን ፡ ዝናመ ፡ ምሕረት ፤
ደግሞም ፡ ለሚሰጠን ፡ እክለ ፡ በረከት ።

ተነሡ ፡ እንዘምር ፡ ...............
ሁሉንም ፡ በጊዜው ፡ ለሚሰጠን ፡ ጌታ ፤
መዘመር ፡ አለብን ፡ ሁላችን ፡ በልልታ ።

ተነሡ ፡ እንዘምር ፡ ...............

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## የምሥራች ፡ ዕልል ፡ በሉ ፡

ያምላካችን ፡ ክብሩ ፡ ይስፋ ፤
ምሥጋናውም ፡ ይንሰራፋ ፤
ሰይልናልና ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፤
ወገኖቼ ፡ እንዳንጠፋ ።

የምሥራች ፡ ዕልል ፡ በሉ ፤
ችግረኞች ፡ ድሆች ፡ ሁሉ ፤
የምሥራች ፡ ዕልል ፡ በሉ ።

ተሰናዱ ፡ በውል ፡ ሁኑ ፤
እንድንዘምር ፡ ለሕጻኑ ፡
ወርዶ ፡ መጥቶዋል ፡ ከዙፋኑ ፤
ቤዛ ፡ ሊሆን ፡ ለወገኑ ።

የምሥራች ፡ ...............

አምላካችን ፡ ደግ ፡ አባት ፤
ባለ ፡ ብዙ ፡ ቸርነት ፤
ወገኖቼ ፡ እንዳንሞት ፤
ሰደደልን ፡ መድኃኒት ።

የምሥራች ፡ ...............

የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሆሣዕና ፤
ይገባዋል ፡ ክብር ፡ ምሥጋና ፤
ለርሱ ፡ ችግር ፡ ለኛ ፡ ጤና ፤
ከዙፋኑ ፡ ወርዶዋልና ።

የምሥራች ፡ ...............

ባጎደሉት ፡ ሰዎቻችን ፤
አስሮን ፡ ነበር ፡ ጠላታችን ።
ከፋይ ፡ ሰዶ ፡ ለዕዳችን ፡
ባሮች ፡ ሆነ ፡ ላምላካችን ።

(ከሠራዊተ ፡ ክርስቶስ ፡ ማኅበር) ።



## አምላካችንን ፡ እንለምን ፡

አቤቱ ፡ ጸሎቴን ፡ ስማኝ ፡ ፊትህንም ፡ መልስ ፡
ወደ ፡ እኔ፤

ሁል ፡ ጊዜ ፡ የምበድልህ ፡ ፍጡርህ ፡ ነኝ ፡ አት
ጣለኝ ፡ ወደማያልፍ ፡ ኩነኔ ።

መሐሪ ፡ ርኅሩኅ ፡ ነውና ፡ ለዘለዓለም ፤
ምንም ፡ የሚሳነው ፡ የለም ።

ተነሡ ፡ እንቅረብ ፡ ባንድነት ፡ ሁነን ፡ እንሳተፍ፡
ከጸጋው ፡

ኑ ፡ እንለምነው ፤ አምላካችንን ፡ በንጹሕ ፡ ልብ ፡
እንደብለቅ ፡ ከመንጋው ።

መሐሪ ፡ ርኅሩኅ ፡ ነውና ፡ ለዘላለም ፤
ምንም ፡ የሚሳነው ፡ የለም ።

በሰማይ ፡ ላለው ፡ ፈጣሪያችን ፡ እንገዛለት ፡በቅን ፡
ሁነን ፤

እንለምነው ፡ እንቅረበው ፡ ሁላችንም ፡ በመን
ግሥቱ ፡ እንዲያስበን ።

መሐሪ ፡ ርኅሩኅ ፡ ነውና ፡ ለዘላለም ፤
ምንም ፡ የሚሳነው ፡ የለም ።

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፳፰ ፤

## አቤቱ ፡ ምሕረትህን ፤

አቤቱ ፡ ምሕረትህን ፡ ከኔ ፡ አታርቅብኝ ፤
ቸርነትህና ፡ ይቅርታህ ፡ ይጎብኙኝ ፤
ኃጢአቶቼም ፡ ያዙኝ ፡ ማየትም ፡ ተሳነኝ ፤
እንደራሴ ፡ ፀጉር ፡ በላዬ ፡ ከበቡኝ ፤
እንዳልቀር ፡ ወድቄ ፡ በደሌ ፡ ጨልሞኝ ፤
የደኅነቴ ፡ ፋና ፡ አምላኬ ፡ አንተ ፡ ሁነኝ ።

መዝሙር ፡ ፳፱ ፤

## እንደ ፡ ቸርነትህ ፡

እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ አቤቱ ፡ ማረኝ ፤
እንደ ፡ ምሕረትህም ፡ ይቅርታን ፡ ስጠኝ ።

ከኃጢአቴም ፡ አንጻኝ ፡ ከብዙ ፡ በደሌ ፤
ለዚያች ፡ ከፉ ፡ ኃጢአት ፡ እንዳልሆናት ፡ ሎሌ ።

እኔም ፡ አመጻዬን ፡ በደሌን ፡ ሳውቀው ፤
ከቶ ፡ የሚያድነኝ ፡ ቸርነትህ ፡ ነው ።

አንተን ፡ ብቻ ፡ በደልሁ ፡ ክፉም ፡ አደረግሁ ፤
አሁን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ከፊትህ ፡ ወደቅሁ ።

ከፊትህ ፡ ወድቄ ፡ ስለምን ፡ አንተን ፤
መውደቄን ፡ ተመልከት ፡ አምላክ ፡ ብርሃን ።

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ፡ ፴ ፤

## መቃብሬ ፡

መቃብሬ ፡ እኔን ፡ ይጠብቃል ፤
እንዳልገባ ፡ ልቤ ፡ ኋላ ፡ ቀርቷል ፤
መድኃኒቴን ፡ ለማግኘት ፡ ይጓጓል ።
እንዳልሞት ፡ ሳላገኝ ፡ መድኃኒቴን ፡ መድኃኒቴን ፤

ሳላገኘው ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒቴን ፤
ሳላወርደው ፡ ክፉውን ፡ ኃጢአቴን ፤
መቃብሬ ፡ ታገስ ፡ አደራህን ፤
እንዳልሞት ፡ ሳላገኝ ፡ መድኃኒቴን ፡ መድኃኒቴን ።

መዝሙር ፡ ፴፩ ፤

## አታውኪኝ ፡ ነፍሴ ፤

አታውኪኝ ፡ ነፍሴ ፡ አታስጨንቂኝ ፤
በዓለም ፡ መድኃኒት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመኝ ፤
ዋልያ ፡ እንደሚናፍቅ ፡ ወደ ፡ ውሀ ፡ ምንጮች ፤
አቤቱ ፡ ወደአንተ ፡ ነፍሴ ፡ ናፈቀች ፤

አታውኪኝ ፡ ...............
መቼ ፡ ተነስቼ ፡ መቼ ፡ እደርሳለሁ ፤
ያምላኪንስ ፡ ፊቱን ፡ መቼ ፡ እየዋለሁ ።

አታውኪኝ ፡ ...............
የሕይወትን ፡ ውሃ ፡ እያስታወሰችኝ ፤
ነፍሴም ፡ ወደሕያው ፡ አምላክ ፡ ተጠማች ።

አታውኪኝ ፡ ...............

www.ethiopianorthodox.org

## በሰማይ ፡ እስክንገናኝ ።

አምላክ ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ይሁን ፤
ወትሮም ፡ በምክሩ ፡ ይምራችሁ ፤
በፍቅሩም ፡ ይሸከማችሁ ፤
እስክንገናኝ ፡ በኢየሱስ ፡ ፊት ።

በሰማይ ፡ በሰማይ ፡ በሰማይ ፡ እስክንገናኝ ።
በሰማይ ፡ በሰማይ ፡ በሰማይ ፡ እስክንገናኝ ፤
በኢየሱስ ፡ ፊት ፤

አምላክ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ይሁን ።
ከጉዳት ፡ ይጠብቃችሁ ።
መናም ፡ ከሰማይ ፡ ይስጣችሁ ።
እስክንገናኝ ፡ በየሱስ ፡ ፊት ፤

በሰማይ ፡ በሰማይ ፡ ...............
አምላክ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ይሁን ፡
ፈተና ፡ ሲያስፈራችሁ ፤
በእርሱ ፡ ኃይል ፡ ያጠንክራችሁ ፡
እስክንገናኝ ፡ በየሱስ ፡ ፊት ፤

በሰማይ ፡ በሰማይ ፡ ...............
አምላክ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ይሁን ፤
አትካዱ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማን ፡
ሞት ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ አትፍሩ ፤
እስክንገናኝ ፡ በኢየሱስ ፡ ፊት ።

(ከመሠረተ ፡ ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን) ፤



## የኢትዮጵያ ፡ መዝሙር ፤

ኢትዮጵያ ፡ ሆይ ፡ ሀገራችን ፡ ረስቼሽ ፡ እንደ
ሆነ ፡ ቀኜ ፡ ትርሳኝ ፤

ያላሰብሁሽ ፡ እንደሆን ፡ መላሴ ፡ በትናጋዬ ፡
ይጣበቅ ፤

ከደስታዬ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሆይ ፡
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ባላደረግሽ ፤

አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቀን ፡ የጠ
ላቷን ፡ ልጆች ፡ አስብ ፤

አፍርሷት ፡ አፍርሷት ፡ እስከ ፡ መሠረቷ ፡ ድረስ ፡
አፍርሷት ፡ ያሏትን ፤

አንቺ ፡ የተፈታሽ ፡ የጠላታችን ፡ ልጅ ፡ ያደረ
ግሽብንን ፡ ብድራት ፡

የሚመልስብሽ ፡ አምላካችን ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ።

ልጆችሽን ፡ ይዞ ፡ በደንጊያ ፡ ላይ ፡ የሚደቁሳ
ቸው ፡ ንጉሣችን ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

ኢትዮጵያ ፡ ሆይ ፡ ሀገራችን ፡ ረስቼሽ ፡ እንደ
ሆነ ፡ ቀኜ ፡ ትርሳኝ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ ።


መዝሙር ፡ ፩ — ስብሰባችንን ፡ ባርክልን ፡

» ፪ — አባታችን ፡ ሆይ ፡

» ፫ — የእመቤታችን ፡ ምስጋና ፡

» ፬ — የዘመናት ፡ ጌታ ፡

» ፭ — ደስ ፡ ይበለን ፡

» ፮ — ንጉሥ ፡ ተወለደ ፡

» ፯ — ሐዲጎ ፡ ተሰዓ ፡

» ፰ — አስተርአየ ፡ ገሃደ ፡

» ፱ — ከመ፡ቶ ፡ በግ ፡ አንዱ ፡

» ፲ — እሰይ ፡ ተወለደ ፡

» ፲፩— የዓለምን ፡ በደል ፡

» ፲፪— የጥምቀት ፡ መዝሙር ፡

» ፲፫— ሆሣዕና ፡

» ፲፬— የስቅለት ፡ መዝሙር ፡

» ፲፭— አምላክ ፡ ለኛ ፡ ብሎ ፡

» ፲፮— የትንሣኤ ፡ መዝሙር ፡

» ፲፯— በጎቼን ፡ አውቃለሁ ፡

» ፲፰— ልባችሁ ፡ አይደንግጥ ፡

» ፲፱— ከክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ የሚለየን ፡ ማነው ፡

» ፳ — አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡


# ማውጫ ።


መዝሙር ፡ ፳፩— ቃል ፡ ሥጋ ፡ ለበሰ ፡

» ፳፪— ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡

» ፳፫— ስብሐት ፡

» ፳፬— በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡

» ፳፭— ተነሱ ፡ እንዘምር ፡

» ፳፮— የምስራች ፡ ዕልል ፡ በሉ ፡

» ፳፯— አምላካችንን ፡ እንለምን ፡

» ፳፰— አቤቱ ፡ ምሕረትህን ፡

» ፳፱— እንደ ፡ ቸርነትህ ፡

» ፴ — መቃብሬ ፡

» ፴፩— አታውኪኝ ፡ ነፍሴ ፡

» ፴፪— በሰማይ ፡ እስክንገናኝ ፡

» ፴፫— የኢትዮጵያ ፡ መዝሙር ፡


www.ethiopianorthodox.org